# ኢዴአፓ-መድህን የተሻለ አማራጭ ሆኖ ለሕዝብ ይቀርባል!

ፓርላማ ወይም ምክር ቤት በሕዝብ የተመረጡ ተወካዮች በሕዝብ ስም ውሳኔ የሚሰጡበት የመንግሥት ህግ አውጭ አካል ነው። አንድ የፖለቲካ ፓርቲ ይዞት የተነሳውን ዓላማ ለማስፈጸም የሚችለው በተለያዩ ደረጃዎች ባሉ ምክር ቤቶች አብላጫ መቀመጫዎችን በሕዝብ ይሁንታ አሸናፊ ሲሆን ነው።

በምርጫ ሂደት ማሸነፍና መሸነፍ የሚጠበቅ ውጤት ነው። በዚህም ሂደት አሸናፊው ሕዝብ የሰጠውን ውክልና ተቀብሎ የማስተዳደር ኃላፊነቱን ሲረከብ፤ ተሸናፊው ወገን ደግሞ ያሉትን አነስተኛ መቀመጫዎች ይዞ የገዥውን ፓርቲ ፖሊሲዎችና የአፈፃጸም ጉድለቶች እየተቸ በቀጣይ ምርጫ አሸናፊ ለመሆን የሚያበቃውን የፖለቲካ ሥራ መስራቱን ይቀጥላል። ይህ የትግል ስልት በየትም ሀገር ያሉ የፖለቲካ ኃይሎች እየሰሩበት እንደሆነም ይታወቃል።

ምርጫን የትግል ስልት አድርጐ የተደራጀው የሀገራችን የፖለቲካ ትግል ረጅም ዕድሜን ያላስቆጠረና በልምድ ያልታገዘ በመሆኑ በምርጫ ሂደት ሙሉ ለሙሉ ከማሸነፍ በመለስ ያሉትን ውጤቶች ለመቀበል በፖለቲካ መሪዎች በኩል ከመርግ የከበደ መሆኑን በ1997 ዓ.ም ከተደረገው ምርጫ በኋላ የነበረው ሁኔታ ያረጋገጠው እውነታ ነው።

ምርጫ ሲነሳ ኢዴአፓ-መድህን የሚያሳስበው ዓብይ ጉዳይ በምርጫው ውጤት አሸናፊ ሆኖ ሥልጣን ላይ መውጣቱ ሳይሆን፣ የምርጫው ሂደት በሀገሪቱ የምርጫ ህግ መሠረት ፍፃሜ ማግኘቱና ዓለም አቀፍ ደረጃውን በጠበቀ ሁኔታ መከናወኑ ነው።

በ1997 ዓ.ም በሀገራችን የተካሄደው ምርጫ ጉድለቶች የታዩበት ከመሆኑም በላይ፣ ዓለም አቀፍ የምርጫ አፈፃፀም መርሆዎችን በጣሰ አሰራር ኮረጆ ተቀዶ የሕዝብ ድምፅ የተሰረቀበት እንደነበር የምርጫ ታዛቢዎች ጭምር ምስክርነት የሰጡበት መሆኑ ይታወሳል። በዚህ ወቅት ኢዴአፓ-መድህን "ፓርላማ የምገባው አሸናፊነቴን የሚያረጋግጥ የመቀመጫ ቁጥር ሲኖረኝ ነው" የሚል ለዴሞክራሲ ሥርዓት ግንባታ ፋይዳ የሌለው ቅድመ ሁኔታን ሳይከተል፣ የምርጫው ሂደት እንከን ቢኖርበትም በሕዝብ ይሁንታ ያገኛቸውን ጥቂት የምክር ቤት መቀመጫዎች ተቀብሎ በፌደራሉ የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት፣ በአማራ፣ በሐረሪ፣ በደቡብ እና በኦሮሚያ ክልል ምክር ቤቶች አግባብ ያለው ተሳትፎ በማድረግ ላይ ይገኛል።

በዚህም መሠረት፣ በሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ቀደም ሲል ወጥቶ የነበረው ደንብ የምክር ቤት አባላት ገንቢ ተሳትፎ እንዲያደርጉ በሚረዳ መልኩ እንዲሻሻል የበኩሉን ጥረት አድርጓል። ይህ ደንብ ሲሻሻል በአደረጃጀት ደረጃ አጀንዳዎችን በስምምነት የሚያፀድቅና የምክር ቤቱን ጽህፈት ቤት ሥራ የሚከታተል ሁሉም ፓርቲዎች የተወከሉበት የምክር ቤት ጉዳዮች አማካሪ ኮሚቴ የመንግሥትን ወጪዎችና ፖሊሲዎች አፈፃፀም የሚቆጣጠር በተቃዋሚ ፓርቲዎች የሚመራ የመንግሥት ወጪ አስተዳደርና ቁጥጥር ቋሚ ኮሚቴ፣ ፓርቲዎች በተጠሪዎች እንዲመሩና ቢሮም እንዲኖራቸው፣ ተቃዋሚዎች በወር አንድ ጊዜ አጀንዳ የሚያቀርቡበት የተቃዋሚዎች ቀን፣ በሳምንት አንድ ጊዜ ሚኒስትሮች በወር አንድ ጊዜ ጠቅላይ ሚኒስትሩን በተለያዩ

ጉዳዮች ዙሪያ ለመጠየቅ የሚያስችል የጥያቄ ጊዜ፣ የመሳሰሉትን አደረጃጀቶች እንዲያካትት ተደርጓል፡፡ በሁሉም ቋሚ ኮሚቴዎች የተቃዋሚ ፓርቲ አባላት እንዲካተቱ መደረጉና ምክር ቤቱ በሚያከናውናቸው በተለያዩ ጉዳዮች ሁሉ የተቃዋሚ ፓርቲ አባላትን ስብጥር ግመት ውስጥ ባስገባ መልኩ እየሰራ መሆኑ የደንቡ መሻሻል በአሰራር ደረጃ ያስገኛቸው በጐ ሁኔታዎች ናቸው፡፡

እነዚህ የአደረጃጀትና የአሰራር መሻሻሎች የሕዝብ ጥያቄዎችን በምክር ቤቱ ባለው መድረክ እንዲደመጡ ለማድረግ ዕድል የሚሰጥ ነው፡፡ የገዥው ፓርቲ አባላትና የተለያዩ ተቃዋሚ ፓርቲ አባላት በተለያዩ ኮሚቴዎች በጋራ የሚሰሩበት ሁኔታ መፈጠሩ በሀገራችን የተጀመረው የዴሞክራሲ ሥርዓት ግንባታ መሠረት እንዲይዝና የመቻቻል ፖለቲካ እየተለመደ እንዲመጣ ዕድል የሚሰጥ ከመሆኑም በላይ ፤ በአንድ ሀገር ያሉ የተለያየ ዓላማ ያላቸው ፓርቲዎች በሀገራዊ አጀንዳዎች ዙሪያ በጋራ የመስራት ባህልን እንዲያዳብሩ ይረዳል የሚል እምነት አለን፡፡

ኢዴአፓ-መድህን በ97ቱ ምርጫ አሸናፊ የሆነባቸውን ጥቂት መቀመጫዎች ይዞ ፓርላማ በመግባቱ ከገዥው ፓርቲ ጋር በተለያዩ ሀገራዊ አጀንዳዎች ዙሪያ ለመወያየትና ለመደራደር ዕድል ሰጥቶታል፡፡ በዚህም መሠረት በአዲሱ የምርጫ ህግና ምርጫ ቦርድ ማቋቋሚያ አዋጅ ላይ ሰፊ ውይይትና ድርድር በማድረግ ለዴሞክራሲ ሥርዓት ግንባታ የሚረዱ አንቀፆች እንዲካተቱ ከማድረጉም በላይ ገለልተኛ የቦርድ አባላትን በመምረጡ ሂደትም ተሳትፏል፡፡ ከዚህ በተጨማሪ በፖለቲካ ፓርቲዎች ማቋቋሚያ አዋጅ ላይ በተፈጠረው የድርድር መድርክ የተሳተፈ ሲሆን፤ በቀጣይም በፕሬስ አዋጅ እና በሌሎች ጉዳዮች ዙሪያ ውይይትና ድርድር ሲደረግ የበኩሉን ጥረት ያደርጋል፡፡

በአጠቃላይ፣ ፓርላማም ሆነ በተለያዩ ደረጃዎች የሚገኙ ምክር ቤቶች ለሠላማዊ የፖለቲካ ትግል እጅግ ጠቃሚ መድረኮች መሆናቸውን ኢዴአፓ-መድህን ያምናል፡፡ በመሆኑም፣ በመጪው ሚያዚያ ወር በሚካሄደው የአካባቢ ምርጫ የኢዴአፓ-መድህን ፓርቲ ዕጩዎች የሕዝብ ይሁንታ አግኝተው ቢያሸንፉ፣

- በፓርላማ የወጣው የአሰራርና የአባላት ሥነ-ምግባር ደንብ ላይ ያሉ አደረጃጀቶችና አሰራሮች በየደረጃው ባሉ ምክር ቤቶች ደረጃ እንዲካተቱ በማድረግ በሀገሪቱ የተጀመረው የመድብለ ፓርቲ ሥርዓት እንዲጠናከር የበኩላችንን ጥረት እናደርጋለን፣

- በየደረጃው ባሉ ምክር በቶች ባሉ አባላት አማካይነት ድርድርና ውይይት በማድረግ በሀገሪቱ የመቻቻል ፖለቲካ መሠረት እንዲይዝና የተለያየ አመለካከት ያላቸው የፖለቲካ ፓርቲ አባላት በአገራዊ አጀንዳዎች ዙሪያ በጋራ የመስራት ባህል እንዲዳብር የበኩላችንን ጥረት እናደርጋለን፣

- ከዚሁ ጋር ተይዞ ከምርጫ በኂላ ሕዝብን ለእልቂት ንብረትን ለውድመት የሚዳርግ አላስፈላጊ ውዝግብ እንዳይፈጠር፣ ከተፈጠረም ጉዳት ሳይደረስ ለሕዝቡ ቅርብ በሆኑ መድረኮች አማካይነት ድርድርና በውይይት ለመፍታት የበኩላችንን ጥረት እናደርጋለን፣

- የሕዝብ ጥያቄዎችን በየደረጃው ባሉ ምክር ቤቶች በማቅረብ እንዲመጡና አግባብ ባለው የመንግስት አካል መፍትሄ እንዲበጅለት ጥረት እናደርጋለን፣

ስለሆነም፣

- በሀገራችን የፖለቲካ ፍጥጫ እንዲያበቃና የመቻቻል ፖለቲካ እንዲጠናከር የኢዴአፓ-መድህንን ዕጩዎች ይምረጡ!

- የልማት የዴሞክራሲና የማህበራዊ ጉዳይ ጥያቄዎች እንዲደመጡ የኢዴአፓ-መድህንን ዕጩዎች ይምረጡ!

- ዛሬም የምርጫ ምልክታችን የድል ምልክት የሆኑት ሁለት ጣቶች ናቸው!

- ኢዴአፓ-መድህን በሠላማዊ ትግሉ ብፅናት ይቀጥላል!